# የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን

## የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ደህንነት ስጋት ግምገማ፣ አስተዳደርና ተግባቦት መመሪያ 291/2013

ሰኔ 2011 ዓ.ም

አዲስአበባ

## ማውጫ


ማውጫ ............ i

መግለጫ ............ 1

1. አጭር ርዕስ ............ 3

2. ትርጓሜ ............ 3

3. የመመሪያዉ ዓላማ ............ 7

4. የተፈጻሚነት ወሰን ............ 7

5. አጠቃላይ ከሙያ ደህንነት ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎች ............ 8

6. የሙያ ደህንነት አደጋ ትንተና አጠቃላይ ታሳቢዎች ............ 8

7. የአደጋ ትንተና ሂደትን ስለመጀመር ............ 9

8. የክስተት ደረጃ ስለማውጣት ............ 10

9. የሙያ ደህንነት አደጋ ግምገማ መረጃ ክምችት ፋይል ............ 12

10. የአደጋ ግምገማ ሂደት ............ 12

1. የጉዳት ምንጭ ልየታ ............ 13

2. የጉዳት ምንጭ ባህሪ ትንተና ............ 13

3. የተጋላጭነት ግምገማ ............ 13

4. የአደጋ ባህሪትንተና ............ 14

5. ሪፖርት ስለማቅረብ ............ 14

11. የሙያ ደህንነት አደጋክስተት አመራር/አስተዳደር ............ 15

1. አጠቃላይ ታሳቢዎች ............ 15

2. የአደጋክስተት አመራር/አስተዳደርአማራጮችን ማየት ............ 16

3. የተለዩ የአደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር አማራጮችን ስለመተግበር ............ 16

4. ስለአደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደርእርምጃዎች ወጤት ክትትልና ግምገማ ............ 16

5. የመካከለኛና ከፍተኛ የሙያ ደህንነት አደጋ ክስተቶች አመራር/አስተዳደር ............ 17

6. የመካከለኛ ደረጃ የሙያ ደህንነት አደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር ............ 17

7. የከፍተኛ ደረጃ (የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ) የሙያ ደህንነት አደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር ............ 18

8. የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ማስተባበርያ ክፍልአባላት ጥንቅር ............ 18

9. የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ማስተባበርያ ክፍልተግባራት ............ 19

12. የአደጋ ክስተት ኮሚኬሽን ............ 19

1. የሙያ ደህንነት አደጋ ክስተት ኮሚኬሽን ታሳቢዎች ............ 19

2. በመደበኛ ሁኔታ ስለሚኖር የመረጃ ልወወጥ ............ 20

3. በመካከለኛና በከፍተኛ የመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት ወቅት ስለሚኖር የመረጃ ልውውጥ አጠቃላይ ማምሪያ ...20
4. የመረጃ ልውውጥ መንገዶች ...21
5. ስለሚሰጥ መግለጫ ይዘት ...22
13. ክትትልና ግምገማ ...22
14. የመኖ ደህንነት አደጋ ትንተና እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት ...23
ለመኖ ደህንነት አደጋ ትንተና ድጋፍ የአቅም ግንባታ ...24
15. የባለስልጣኑን አቅም ስለመገንባት ...24
16. የባለድርሻ አካላትን አቅም ስለመገንባት ...24
17. ተፈፃሚነት ስለሚኖራቸው መመሪያዎች ...24
18. መመሪያውን ስለማሻሻል ...25
19. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ...25

## መግለጫ

በሀገር ውስጥ የሚመረቱ፣ ከሀገር ወደ ውጭ የሚላኩ፣ ከውጭ ወደ ሀገር የሚገቡ መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ጥራትና ደህንነት በማረጋገጥ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ተጠቃሚዎችስለ ኢትዮጵያ እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅዖ ጥራትና ጤናማነት ዋስትና በመስጠት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ በማድረግ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ኢትዮጵያ የግብርና ውጤቶች ከፍተኛ የደህንነት ደረጃ አስገዳጅ በሆነበት የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ሆና በሰፊው የዓለም ገበያ ለመሳተፍ በሂደት ላይ መሆንዋና ለዚህም የድርጅቱን የጥራትና ደህንነት ደረጃ የጠበቀና ለጤና ተስማሚ የሆነ መኖ አቅርቦትን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በሀገር ውስጥ የሚመረተውን፣ ከውጭ ወደ ሀገር የሚገባውን፣ የሚከፋፈለውን፣ ወደ ውጭ የሚላከውንና የሚቸረቸረውን፣ እንዲሁም ጥቅም ላይ የሚውለውን መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራትና ደህንነት በማረጋገጥ የቀጥተኛ ተመጋቢውን እንስሳ ደህንነት፣ የእንስሳት አርቢዎችን ከኢኮኖሚያዊ ጉዳት፣ የእንስሳት ምርት ተጠቃሚውን ህብረተሰብ እንዲሁም የአካቢ ጤናን ማጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ወደ ሀገር የሚገባ መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠና አስፈላጊ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑና ደህንነቱና ደረጃውን ያልጠበቀ የእንስሳት መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርትና ሽያጭን እንዲሁም ማንኛውንም ከመኖ ጋር በተያያዘ የሚካሄድ የማጭበርበር ተግባር መከላከል የሚያስችል የግብይት ሥርዓት ማዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከምርት እስከ አጠቃቀም ያለውን የመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃን ጥራትና ደህንነት ትንተና ሂደት ለመምራትና ለመከታተል የሚያግዙ ተቀባይነት ያላቸው መስፈርቶችን በማስቀመጥ ለክትትልና በሀገር ውስጥ መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ የሚያመርቱ፣ ከውጭ ወደ ሀገር የሚያስገቡ፣ የሚያከፋፍሉ፣ ወደ ውጭ የሚልኩ፣ የሚቸረችሩ፣ እንዲሁም መኖን የሚጠቀሙ አካላት አሰራራቸውን እራሳቸው እንዲከታተሉ በማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ መኖና ብሎም ምግብ ጥራትና ደህንነት እንዲጠበቅ ማስቻል፣ ከመኖ ጋር የተያያዘ ድንገተኛ የደህንነት አደጋ ሲፈጠር የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ሚና መለየት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 ለባለሥልጣኑ በተሰጠው አዋጁንና ከአዋጁ የሚመነጩ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራትና ደህንነት በማረጋገጥ የቀጥተኛ ተመጋቢውን እንስሳ ደህንነት፣ የእንስሳት አርቢዎችን ከኢኮኖሚያዊ ጉዳት ስጋት፣ የእንስሳት ምርት ተጠቃሚውን ህብረተሰብ እንዲሁም የአካባቢ ጤናን መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤ደህንነቱና ደረጃውን ያልጠበቀ የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ግብይትን መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣ይህ የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃዎች የጥራትና ደህንነት ስጋት ግምገማ፤ አስተዳደርና ተግባቦት መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍልአንድ

## አጠቃላይ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህመመሪያ "የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃዎች የጥራትና ደህንነት ስጋት ግምገማ፤ አስተዳደርና ተግባቦት መመሪያ 291/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

በአዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ2 ሥር ለተመለከቱ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁሆኖየቃሉአገባብሌላትርጉም የሚየሰጠዉ ካልሆነ በስተቀርበዚህመመሪያ ወስጥ፡ –

1. **"መኖንወይምመኖጥሬዕቃንመከለስ"**ማለት ጥራትና ደህንነቱ አስተማማኝ ከሆነ ታዋቂ የመኖ ምርት ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት ጋር ተፈላጊወን ደረጃ ከማየሟላ ባዕድ ነገር ጋር መቀላቀል ማለት ነወ፤

2. **ቁጥጥር –** የመኖና ምግብ ደህንነት ክትትል ተግባራትና ተያያዥ ወጤቶቻቸው ከሚፈለገው የደህንነት ሥርዓት ዓላማዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸወን ለማረጋገጥ ነፃ በሆነ አግባብ የሚከሄድ የፍተሻ ሥርዓት

3. **"ባለሥልጣን"**ማለትየእንስሳትመድኃኒትናመኖአስተዳደርናቁጥጥርባለስልጣን ነወ፤

4. **ባዮሎጂያዊ የስጋት ምንጮች፡**ለእንስሳትና ለሰው ጤና ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ እንደ ባክቴርያ፣ ቫይረስ፣ ፈንገስ እና እነዚህ ተህዋስያን የሚየመነጩቸው መርዞችን ያካተተ የስጋት ምንጭ ነው

5. **ኬሚካላዊ የስጋት ምንጮች፡**ለእንስሳትና ለሰው ጤና ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ እንደ ማዕድናት፣ የፀረ ተባይ ቅሪቶች፣ነፃ ጎሲፖል እና ሌሎች ተመሳሳይ ኬሚካሎችን ያካተተ የስጋት ምንጭነው

6. **መግለጫ** አግባብ ባለው ባለሥልጣን በማኛቸወም የስርጭት ዘዴ የሚለቀቅ ኦፊሴላዊ መረጃ

7. **አግባብ ያለው አካል–**በባለሥልጣኑ ቁጥጥርና ክትትል ስር ሆኖ የመኖ ሀይጂንና ደህንነት ጋር የተያያዙ ሥራዎችን እንዲሰራ ዕወቅና የተሰጠው አካል

8. **አግባብ ያለው ባለሙያ –**የሚሰጠወን ተግባር ለማከናወን የባለሥልጣኑን መስፈርት የሚየሟላ ስልጠና፣ዕወቀት፣ ክህሎትና አቅም ያለው ሰው ነው.

9. **"የመኖወይምየመኖጥሬዕቃጤናምስክርወረቀት"–** አንድየመኖወይምየመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት ጤናማ ስለመሆኑና መኖወን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃወን ለሚመገበዉ እንስሳወይምየእንስሳወንምርት ወጤቱንበሚመገቡ ሰዎችላይ የጎንዮሽ የጤና ጉዳት እንደማየስከትል የሚየረጋግጥ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ነወ፤

10. **"የመኖወይምየመኖጥሬዕቃደረጃዎች"**ማለትበኢትዮጵያ የደረጃዎችኤጀንሲ የፀደቀናአፊሴላዊተቀባይነትያገኘ የመኖወይምየመኖጥሬ ዕቃጥራትናደህንነት ደረጃ ነው፤

11. **ጭነት –** በአንድ ኮንትራት ወይንም የመጫኛ ሰነድ በአንድ ጊዜ የሚጓጓዝ የምርት ማጠን

12. **በካይ አካል –** በመኖ ወስጥ ሆን ተብሎ ያልተጨመረ የመኖን ብሎም የምግብ ደህንነትን ሊያጓድል የሚችል ማንኛወም ባዮሎጂያዊ፣ ኬሚካላዊና ሌላ ባዕድ አካል ነው፤

13. **ወሳኝ የቁጥጥር ነጥብ –** በመኖ ወይም በምግብ አመራረት ሂደት የደህንነት አደጋን ለመካላከል፣ ለማስወገድ ወይንም በሚፈለገው ደረጃ ለመቀነስ ቁጥጥር የሚከሄድባቸው ዋነኛ ነጥቦች/ቦታዎች፤

14. **ወሳኝ ገደብ –** በወሳኝ የቁጥጥር ነጥብ ላይ የደህንነት አደጋን ለመካላከል፣ ለማስወገድ ወይንም ለመቀነስ የቁሳዊ፣ ባዮሎጂያዊ ወይም ኬሚካላዊ የአደጋ ምንጮች ሊገደቡበት የሚገባ ዝቅተኛ ወይንም ከፍተኛ የማጠን ወሰን ነው፤

15. **ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ** – ከምግብ/መኖ ጋር የተያያዘ የደህንነት አደጋ ክስተት በዋናና ተያያዥ ምርቶች የሀገር ወስጥና ዓለምአቀፍ ወቅታዊ ሽያጭ እንዲሁም የወደፊት ሽያጭ ላይ የሚኖረው ወጤት፤

16. **የተጋላጭነት ግመማገማ –**የእንስሳት ተዋፅዖ የሚያመርቱ እንስሳት ከመኖ ጋር በተያያዘ ለደህንነት አደጋ ተጋላጭነት ዓይነትና ማጠን እንዲሁም የአደጋው ወደ ምግብ የመዛመት ማጠን ግምገማ

17. **"መኖ"**ማለትበሀገርወስጥየሚመረት፣ከወጭወደሀገር የሚገባ፣ በሀገርወስጥምከአንድክልልወደሌላክልልለንግድየሚዘዋወርወይም ወደወጭሀገርገበያለሽያጭየሚወጣየእንስሳትምግብነው፡ ፡

18. **"የመኖተጨማሪንጥረነገር"**ማለት ማንኛወም መደበኛ የእንስሳት አመጋገብን የንጥረ መኖ ፍላጎት ለማሟላት በይዘቱ የምግብነት ወይም መኖነት ያለዉ ወይም የሌለዉ ሆኖ በመኖ ዝግጅት ወቅት ለማጣፈጫ ለቀለም ማነመሪያ ወይም ለማጣበቂያ (ቅርጽ ማስያዣ) ወዘተ በአነስተኛ ማጠን የሚቀላቀል ንጥረ ነገር ሆኖ በእንስሳት ወይም በእንስሳት ምርት ተመጋቢዎች ላይ ምንም ዓይነት የጎንዮሽ ጉዳት እንደማያስከትል የተረጋገጠ ንጥረ ነገር ነው፤

19. **"የመኖ ግብዓት ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ"**ማለት ተፈላጊወን መሠረታዊ መኖ ለማዘጋጀት የሚያገለግል የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም ተጨማሪ ንጥረ- ነገር ሲሆን የሸንኮራ አገዳና ስኳር ተረፈ ምርት (ቁርጥራጭ፣ ባጋስ፣ ሞላሰስ) ፣ የምግብ ዘይትና የዱቄት ፋብሪካ ተረፈ ምርት (ፋጉሎ፣ ፉሩሽካ፣ ፉሩሽኬሎ፣ ብጣሪ፣ እንቅጥቃጭ፣ የካዛቫ ትርፍራፊ)፣የቢራና የአልኮል ፋብሪካ ተረፈ ምርት (የቢራ አተላ፣የአረቂ አተላ፣የብቅል አሰር)፣ የመኖ ሰብል (እርጥብ፣ድርቆሽ፣የተቀረጣጠፈ፣ፔሌት፣ ወዘተ)፣የእንስሳት ዕርድተረፈ ምርት (ደም፣ አጥንት፣ የስጋና ቆዳ ቅንጥብጣቢ፣አፋል፣ሽሆና፣የዓሳ ተረፈ ምርት፣የዶሮ ኩስ ወዘተ)፣ የመኖ ተጨማሪ ማዕድናት (ኖራ፣ቦሌ፣ዳይአቶማስአፈር፣ጨው ወዘተ)፣ ማይክሮ ባይሎጂካል የመኖ ማሻሻያ ግብዓቶች (ኢፌክቲቭ ማይክሮ ኦርጋኒዝም፣ኢንዛይምስ፣ፕሮባዮቲክስና የመሳሰሉትን) ይጨምራል፤

20. **ጥሩ የግብርና አመራረት ተሞክሮ–** ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ቀጣይነትን ባገናዘበ ሁኔታ ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ ምግብ ለማምረት ተግራዊ የሚደረጉ የግብርና ምርትና ድህረምርት መርሆዎች፤

21. **መልካም ንፅህናን የጠበቀ የአመራረት ተሞክሮ –** የመኖና የምግብን ደህንነትና ተስማሚነት ለማረጋገጥ የሚከናወኑ አስፈላጊ ተግባራት፤

22. **ሚልካም የአሜራረት ተሞክሮ –** በአንድ የሥራ ዘርፍ በተቀማጠ የአሠራር ደረጃ ላይ ተመሥርተው የሚከሄዱ ተግባራት፤

23. **የጉዳት/አደጋ ምንጭ** በጤና ላይ አላስፈላጊ ወጤት ሊያስከትል የሚችል የመኖ ባዮሎጂዊ፣ ኬሚካላዊ፣ ቁስአካላዊ ምንጮች ናቸው፤

24. **የጉዳት ምንጭትንተናና ወሳኝ የቁጥጥር ነጥቦች–**አስፈላጊ ቁጥጥር ካልተካሄደ ትርጉም ያለው የጥራትና የደህንነት ጉድለቶች ሊደርሱ የሚችልባቸው የአሜራረት የስራ ሂደት ደረጃዎች/ነጥቦች ማለያ ዘዴ፤

25. **የጉዳት ምንጭ ባህሪ ግምገማ–**በመኖ ወስጥ የሚገኙ ባዮሎጂዊ፣ ኬሚካላዊ፣ አካላዊ ኩነቶች ጋር የተያያዙ አላስፈላጊ የጤና ወጤቶችን ተፈጥሮ፤ ዓይነትና ማጠን ግምገማሥራ ነው፤

26. **የጉዳት ምንጭማለየት/ልየታ–**በጤና ላይ አላስፈላጊ ወጤት ሊያስከትል የሚችል በተለየ የመኖ ዓይነት ወይንም የመኖ ምድቦች/ዓይነቶች ሊኖር የሚችል ባዮሎጂዊ፣ ኬሚካላዊ፣ አካላዊ ኩነቶች የማለየት ሥራ ሂደትነው፤

27. **ክስተት –**በወቅቱ ባለው መረጃ መሠረት የመኖን ደህንነት ጥርጣሬ ላይ የሚጥልና እርምጃ እንዲወሰድ የሚጋብዝ ማንኛወም አጋጣሚሁኔታ ነው፤

28. **ምርመራ –**በምርት ሂደት ላይ ያለና ያለቀለት መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ፣ የአሜራረትና ስርጭት ሂደት ተገቢ የቁጥጥር ስርአትና ማስፈርቶችን ማሟላታቸወን የሚፈተሽ ሥራ ነው፤

29. **"ገላጭጽሑፍ"**ማለትበመኖወይም በመኖጥሬዕቃ መያዣዕቃላይየሚጻፍወይምየሚለጠፍወይምየሚታሰርሆኖስለመኖዉ ወይምየመኖጥሬዕቃወየሚገልጽ ጽሑፍ ነዉ፤

30. **ሕግ–** ከምግብና መኖ ጋር የተያያዙ የእንስሳትንና የሕዝብን ጤና፣ የሸማቾችን መበት ጥበቃና የፍትሀዊ ንግድ ሂደትን ለማስፈን አግባብ ባላቸው አካላት የሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማስፈርቶች ወይንም የአሠራር ሥርዓቶች ናቸው

31. **ከፍተኛ የፀረ–ተባይ ቅሪት ገደብ –** በኮዴክስ አሊመንታርየስ ኮሚሽን በመኖ ወስጥ ወይም ላይ የተፈቀደወን ከፍተኛ የፀረ–ተባይ ቅሪት ይዘት (በሚግ/ኪግ የሚገለፅየማጠን ወሰን ነው፤

32. **ይፋ ዕወቅና አሰጣጥ –**ባለስልጣኑ የአንድን ተቆጣጣሪ ተቋም የብቃት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ብቃቱን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ነው፤

33. **"የመኖወይም የመኖጥሬዕቃ ማሸጊያወይም መያዣ"**ማለትየእንስሳትመኖ ወይምየመኖግብዓቶችንለመያዝ፣ ለማጓጓዝናለማከማቸት ጥቅም ላይ የሚውል መያዣ ዕቃ ነዉ፤

34. **ቁሳዊ የጉዳት ምንጭ**በእንስሳትና በሰው ጤና ላይ ስጋት የሚሆኑ እንደ ማስታወት፣ ብረታብረት፣ እንጨት፣ ፕላስቲክ፣ ድንጋይና ተመሳሳይ ቁሳዊ ነገሮችን ያካትታል፤

35. **"አዋጅ"**ማለትየእንስሳትመድኃኒትናመኖአስተደደርናቁጥጥርአዋጅቁጥር፤ 728/2004 ነው፤

36. **አሃዛዊ የአደጋ ግምገማ** –በሳይንሳዊ ሂደት ላይ የተማሰረተና የተደራጀ፣ ባዮሎጂያዊ፣ ኬሚከላዊና ፊዚካላዊ የአደጋ ምንጭ ያለው መኖ በመመገብ የሚመጣ ህመም የመከሰት ዕድልና የህመሙ ክብደት መገመት የሚያስችል አህዛዊ መረጃ ነው፤

37. **ዓይነታዊ የአደጋ ግምገማ** –ብዙ ጊዜ የአደጋ አስተዳደር እርምጃ ለመወሰድ ጥቅም ላይ የሚውል አህዛዊ ያልሆነና የአደጋው ክስተት ተጨማሪ ጥናት የሚያስፈልገው መሆን አለመሆኑን የማለየት ሂደት ነው፤

38. **አደጋ** –ከመኖ ጋር በተያያዘ የጉዳት ምንጭ ምክንያት የሚከሰት የጤና ችግር የመከሰት ዕድልና የችግሩ ክብደትነው፤

39. **የአደጋ ትንተና** –ሶስት የሚገናኙ አካላትን (የአደጋ መገምገም፣ አስተዳደርና ተግባቦት/መረጃ ስርጭት) የያዘ የአሠራር ሂደት ነው፤

40. **የአደጋ ግምገማ**– አራት ደረጃዎችን የያዘ ሳይንሳዊ ሂደት፤ (ሀ) የጉዳት ምንጭለየታ(ለ) የጉዳት ምንጭ ባህሪ ትንተና(ሐ) የተጋላጭነት ግምገማ (መ) የአደጋ ባህሪ ትንተና ናቸው፤

41. **የአደጋ ባህሪግምገማ**–የጉዳት ምንጭን በማለየት፣ የጉዳት ምንጭን ባህሪ በመተንተንና የተጋላጭነት ግምገማ ላይ ተማስርቶ በአንድ ሕዝብወይንምመንጋ ወስጥ ያለወንና ሊኖር የሚችለወን አላስፈላጊ የጤና ጉዳትየሚያስከትል አደጋ በዓይነትና በማጠን ግምት ማስላትነው፤

42. **የአደጋ መረጃ ልወውጥ** –በአደጋ ገማምጋሚዎች፣ አመራር ሰጪአካላት፣ ተመጋቢዎች፣ ኢናዱስተሪ፣ የአካደሚ ማሕበረሰብና ሌሎች አካላት መካከለል ከአደጋ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፣ አስተያየቶችን፤ የግምገማ ወጤቶችን፣ የሚሰጡ ወሳኔዎችን በተማለከተ በአደጋ ትንተናው ሂደት በሙሉ የሚደረግ የመረጃልወውጥ ነው፤

43. **የአደጋግምት** –ከአደጋ ልየታና ግምገማ የሚመነጭ የአደጋ ማጠን ግምትነው፤

44. **የአደጋክስተት አመራር/አስተዳደር** –የተጠቃሚን ጤና ጥበቃ፣ ፍትሀዊ ግብይትን ግምት ወስጥ ባስገባ ሁኔታ የተለያዩ የፖሊሲ አማራጮችን በማገናዘብ፣ ከሚመለከታቸወን አካላት ጋር በመመካከር፣ የአደጋ ግምገማ ወጤትን ግምት ወስጥ በማስገባት ለሁኔታው ተፈላጊ አመራር የማስጠት ሂደትነው፤

45. **የአደጋግንዛቤ** –ስለ አንድ አደጋ ባህሪ፣ የመከሰት ዕድል፣ የአስከፊነት ማጠን፣ ሰዎች የሚኖራቸው እሳቤነው፤

46. **የአደጋገፅታ** –ስለተከሰተ የመኖ ደህንነት ችግር መገለጫ የተከሰተበት አግባብወይንም ነፀብራቅነው፤

47. **የመኖ ዝወወር ሰንሰለት ክትትል** –መኖን በጥሬ ዕቃ ምርት ቅብብሎሽ፣ በማቀነባበርና ስርጭት ሂደት፣ ከቦታ ቦታ የሚደረግን የዝወወር ስንሰለት የመከታተል ችሎታ/አቅምና አሠራር ነው፤

48. **የሚፈለጉ ነገሮች** –ማለትበመኖና በመኖ ንጥረ ነገሮች ወስጥ ወይንም ላይ የሚገኙ የእንስሳትን ጤናና የምግብ ደህንነትን አደጋ ላይ በመጣል ለተጠቃሚው የጤና ችግር የሚያስከትሉ በካይና ሌሎች ነገሮችን ያካከትታል፤

49. ማንኛወም በወንድ ጾታየተገለጸወሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የመሜሪያዉ ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ ከመኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን በተሟላከተ ተቆጣጣሪ አካላት ሊከተሉ የሚገባቸዉን አግባብነት ያለዉ የስጋት ግምገማ፣ አስተዳደርና መረጃ አሰጣጥ ሥርዓትበማስቀመጥ የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃን ደህንነት አስተማማኝነት እንዲጠበቅ በማድረግ ጤናማ እንስሳት ምርትወጤትለህብረተሰቡእንዲደርስ ማስቻል ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሁሉም የመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ አመራረት፣ ክምችትና ስርጭት (ጅምላ፣ ችርቻሮ፣ ወደሀገር ማስገባት፣ ከሀገር ማስወጣት) እና አጠቃቀም ሂደት በሚኖር የስጋት ትንተና ሁሉ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ መመሪያው ለውሳኔ አሰጣጥ ድጋፍ የሚሆኑ ከመኖ ጋር የተያያዙ የስጋት ትንተና የሥራ ሂደት መሠረተ ሐሳብን፣ ሀላፊነትንና ሥርዓትንም ያስቀምጣል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሜዳ ደህንነት አደጋ ትንተና

### 5.አጠቃላይ ከሜዳ ደህንነት ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎች

1. የሜዳ ደህንነት ድንጋጌዎችበኢትዮጵያ የሜዳ ደረጃዎች እንዲሁም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ወይንም በሥራ ላይ ያዋለቻቸው ዓለም አቀፍ ደረጃዎች ናቸው
2. ደህንነቱ ያልተጠበቀ ሜዳ ለገበያ ወይንም ለሰው ምግብነት የሚውሉ የእንስሳት ውጤቶችን ለሚያመርቱ እንስሳት ምግብነት አይውልም፡፡በሚከተሉት ሁኔታዎች ሜዳ ደህንነቱ ያልተተበቀ ተብሎ ይቆጠራል፡-
   ሀ) በእንስሳት ብሎም በሰው ጤንነት ላይ አላስፈላጊ ውጤት የሚያመጣ ሆኖ ሲገኝ፣
   ለ) የእንስሳት ምርት ለሰው ፍጆታ ተስማሚ እንዳይሆን የሚያደርግ ሲሆን
3. በሌላ ዝርዝር ዳሰሳ የተለየ መረጃ እስካልተገኘ ድረስ የአንድ ክምችት፣መደብ ወይም እሽግ አካል የሆነ ሜዳ የደህንነት ደረጃወን የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ ክምችቱ፣መደቡ ወይም እሽጉ በሙሉ የደህንነት ደረጃወን እንዳላሟላ ይቆጠራል፡፡
4. የደህንነት ደረጃን ያሟላ ሜዳ ሲባል ደህንነቱ ለደህንነት ማረጋገጫው ግምት ወስጥ ለገቡት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡፡
5. ሜዳ በተወሰነ ሜኢቀፍ የደህንነት ደረጃን የሚያሟላ ቢሆንም ሜዳው የደህንነት ችግር ያለበት መሆኑን የሚያስጠረጥር ምክንያት ሲኖር ባለስልጣኑ ይህንን ሜዳ ወደ ግብይት እንዳይገባ ማድረግ፣ ከግብይት ሂደት እንዲወጣ ማድረግ ይችላል፡፡

### 6.የሜዳ ደህንነት አደጋ ትንተና አጠቃላይ ታሳቢዎች

1. የእንስሳ፣ የሰውና የአካባቢ ጤናን በተገቢው ደረጃ ለማጠበቅ ያለመ የሜዳ ደህንነት እርምጃ ሁኔታውንና የሚወሰደውን እርምጃ ያገናዘበ የሜዳ ደህንነት አደጋ ትንተና ላይ መመስረት አለበት፡፡
2. የአደጋ ግምገማ በወቅታዊ ሳይንሳዊ ማስረጃ ላይ የተመሰረተና ነፃ፣ተጨባጭናግልፅ በሆነ መንገድ መካሄድ አለበት፡፡
3. የሜዳ ደህንነት አደጋ ሁኔታ ከአደጋ ነፃ ከሆነ ሁኔታ እስከ አስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሊደርስ የሚችል ሲሆን አደጋው ለእንስሳትና ብሎም ለሰው ጤና የሚያስከትለው የስጋት ደረጃ መረጃ እስከሚሰበሰብ ድረስ ግልፅ ላይሆን ይችላል፡፡
4. የሜዳ ደህንነት ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑና ተጓዳኝ አካላቱ ለአደጋ ጊዜ ምላሽ ለማስጠት የሚያስችል የተለያዩ አካላትን ሀላፊነትና ተግባር የሚገልፅ ዝርዝር የያዘ፣ አካላቱ በግልፅ የሚረዱት፣ ድግግሞሽንና አሻሚ ያልሆነ ምላሽ አሰጣጥ ዕቅድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
5. የሜዳ አደጋ ትንተና በሚከተሉት ተከፍሎ ስርዓት ባለው ሁኔታ መካሄድ አለበት፡-

**ሀ) የአደጋ ግምገማ** የመኖ ደህንነት ችግር መኖሩ ሲታወቅ በተጠቃሚዎች ላይ ሊያስከትል የሚችለዎ የአደጋ ደረጃ መገምገም አለበት፡፡ ቀጣይ እርምጃዎች በዚህ የአደጋ ግምገማ ወጤትላይ ስለሚመሰረቱ በዚህ ደረጃ የአደጋወን ሁኔታው ለመረዳት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በወቅቱ ማሰብሰብይገባል፡፡

**ለ) የአደጋሁኔታን አመራር/አስተዳደር** – እንደ ስጋቱ ዓይነት፣ የአደጋው ደረጃ፣ በጤና፣ በኢኮኖሚና በንግድ እንቅስቃሴ ላይ የሚኖረወን ተፅዕኖ ባገናዘበ ሁኔታ ለተከሰተው አደጋ የሚሰጥ ተመጣጣኝ የምላሽአመራር ነው፡፡

**ሐ) የአደጋመረጃ ልወውጥ** – በመኖ ደህንነት አደጋ አመራረር/አስተዳደር ወቅት እንደ ስጋቱ ደረጃ የሚተገበር በአግባቡ የተደራጀ የመረጃ ልወውጥ ሰተራተጂ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ በወቅቱ የተከሰተን አደጋ በስልታዊ አመራረር/አስተዳደር ለማሻሻል እንዲሁም ሌሎችም ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ተመሳሳይ አደጋዎችን ለመቋቋም የሚያስችል ትምህርት በመወሰድ በአደጋው ወቅትና ከአደጋው በኋላ አደጋወን ለመታደግ ስለተወሰዱ እርምጃዎች የሚከሄድ በቂ ዳሰሳ ማካሄድና አግባብ ያለው መረጃ ማለዋወጥ ይገባል፡፡

## 7.የአደጋ ትንተና ሂደትን ስለመጀመር

1. ስለአደጋ መከሰት መረጃ ከተለያዩ ምንጮች ሊገኝ ይችላል፡፡ መረጃው ከመኖ አምራቾች፣ ከመኖ ተጠቃሚዎች ቅሬታ፣ ከመገናኛ ብዙሃን፣ የላቦራቶሪ ወጤቶች፣ በባለስልጣኑ መደበኛ የቁጥጥርና ክትትል ሥራ ሂደት እንዲሁም ከሌሎች ምንጮች ሊገኝ ይችላል፡፡
2. የመረጃ ምንጩ/አቀባዩ መኖ ወይንም የመኖ ጥሬ ዕቃ የደህንነት መስፈርትን እንደማያሟላ ሲያወቅ ስለችግሩ በተቻለ ፍጥነት ለባለስልጣኑ ወይንም ለወኪሉ ማሳወቅ አለበት፡፡
3. የሚሰጠው መረጃ በተቻለ መጠን ዝርዝር ሁኔታዎችን ቢያንስ ግን የችግሩን ባህሪይ/ዓይነት፣ ችግሩ የታየባቸው የመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ዓይነቶች፣ መኖው ለምን ዓይነት እንስሳት እንደታለሙ፣ ጥቅሉን፣ የአምራቹን ሥም እና ምንጭ ማካተት አለበት፡፡
4. የመጀመሪያው የመኖ ደህንነት ስጋት መረጃ እንደተገኘ ወዲያው በቦታው ጉብኝት በማድረግ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ ከዚያም የሚከተሉትን ያካተተ ፍተሻ ይካሄዳል፤ በመኖው/ጥሬ ዕቃው ላይ/ወስጥ የሚጠረጠር የአደጋ ምንጭ መኖር አለመኖር፣ የተከሰተ የጤና ችግር መኖር አለመኖሩ፣ የችግሩ ሽፋን፣ የስጋት ምንጩ ማለየት አለማለየቱ፣ ችግር አለበት ተብሎ የተጠረጠረው መኖ/ጥሬ ዕቃ ስርጭት፣ ጊዜያዊ እርምጃዎች የመወሰድ አስፈላጊነት፡፡
5. አደጋው መኖሩ እንደተረጋገጠ የመኖ ደህንነት ምላሽ አሰጣጥ ዕቅድ መሠረት ወደ ተግባር ይገባል፤ የአደጋው ደረጃ በሚጠይቀው መሰረት በባለስልጣኑ ወስጥ ካሉ ዳይሬክቶሬቶች፣ ሌሎች መስሪያ ቤቶችን ያካተተ አስተባባሪ ቡድን ይቋቋማል፡፡
6. በባለስልጣኑ የተሰየመው ቡድን የአደጋወን ጉዳት ለመቆጣጠር ወዲያው የግምገማና ሌሎች እርምጃዎችን የመወሰድሂደት ወስጥ ይገባል፡፡

7. ችግሩ የተከሰተበት ሜዳ ወይንም የሜዳ ጥሬ ዕቃ በዓለም አቀፍ ገበያ የሚሸጥ ከሆነ የላኪው ሀገር ምርቱን ወደ ሀገራቸው ለሚያስገቡ ሀገራት ቢያንስ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት፤ የሚሰጠው መረጃም የተቻለውን ያህል ዝርዝር መሆን አለበት፡፡

## 8. የክስተት ደረጃ ስለማውጣት

1. ለችግሩ ደረጃ የሚመጥን የአደጋ አመራረር/አስተዳደር አማራጮችንና የመረጃ ልውውጥ ስተራትጂን ቀድሞ ለማየት የሜዳ ደህንነት አደጋን በደረጃ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፤
2. የአደጋውን ደረጃ ለማውጣት ለአደጋው ክብደት አስተዋፅዖ ለሚያደርጉ ምክንያቶች አሀዛዊ የነጥብ አሰጣጥ ሥርዓት በማጠቀም አሀዛዊ ማለኪያ ማጠቀም ይቻላል፤ ይህ አሰራር የሚከተሉትን ግብዓቶች ሊያካትት ይችላል፡ -
   - ሀ) በእንስሳትና በእንስሳት ተዋፅዖ ተጠቃሚ ጤና ላይ የሚያስከትለው ወጤት
   - ለ) የተጎጂ እንስሳትና ሰዎች ቁጥር
   - ሐ) የተጋላጭ አካላትዝርዝር
   - መ) የማህበረሰቡ ግንዛቤ ሁኔታ
   - ሠ) በሜዳ/ምግብ ሰንሰለት ወስጥ ያለው ስርጭት
   - ረ) የማስፋፋት/ወስብስብነት ግምት
   - ሠ) የኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ግምት

3. የአደጋው ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜና ከቦታ ቦታ ሊለዋወጥ ስለሚችል ባለስልጣኑ የክስተቱን ደረጃ በየጊዜው እየገመገመ ይከልሳል፡፡ በዚህ መመሪያ የሜዳ ደህንነት ችግር ክስተቶች ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ በሚል ተከፍለዋል፤
   - **ሀ) ዝቅተኛ (ቀላል) ክስተት:-** በእንስሳት ጤና ላይ ሕክምና የማያስፈልገው ቀላል ወጤት ያለው ክስተት፣ ዝቅተኛ የማህበረሰብ የስጋት ደረጃ፣ የሜዳና የእንስሳት ተወፅዖ ሽያጭ ላይ አነስተኛ ተፅዕኖ ያለው ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ያለ ክስተት እንደተለመደ ሁኔታሊቆጠር የሚችልና በባለስልጣኑ መደበኛ አሰራርና ግብዓት ሊሸፈን የሚችልና የተለየ አስተዳደራዊ እርምጃና መረጃ ልውውጥ የሚፈልግ አይደለም፡፡
   - **ለ) መካከለኛ (ከባድ) ክስተት:-**ብዛት ያላቸው እንስሳት ላይ የጤና ችግርና ጥቂት ሞትም ጭምር ሲከሰትና የሕክምና ትኩረት የሚያስፈልገው ክስተት ሲሆን፣ ሰፊ ስርጭት ሊኖረው ይችላል፣ መካከለኛ የማህበረሰብ የስጋት ደረጃ፣ ማጠነኛ የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረት የሳበ፣ የሜዳና የእንስሳት ተወፅዖ ሽያጭ ላይ የሚታይ ተፅዕኖ ያለወና ወደነበረው ሁኔታ ለመመለስ ትልቅ ወጪ የሚጠይቅ፡፡ በዚህ ደረጃ ያለ ክስተት በባለስልጣኑ ወስጥ ሁኔታውን የሚከታተል ልዩ አስተባባሪ ግብረ ኃይል ማቋቋምና ከሌሎችም ተቋማት ጋር በትብብር ማሰራትን ይጠይቃል፡፡

**ሐ) ከፍተኛ (የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ) ክስተት፡-**ብዛት ባላቸው እንስሳት ላይ ከፍተኛ የጤና ችግርና ሞት በስፋት ሲከሰትና ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሰፊ ስርጭት ያለው፣ በሰው ጤና ላይም ችግር ሊያስከትል የሚችል፣ በማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ ስጋት የደቀነ፣ ከፍተኛ የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረት የሳበ፣ የምግና የእንስሳት ተወፅዖ ሸያጭ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያለውና የንግድ ተቋማት ላይ ከፍተኛ ኪሳራና ማዛጋት የሚያስከትል ሲሆን ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ያለ ክስተት ከባለስልጣኑ አቅም በላይ ስለሚሆን ሁኔታውን የሚከታተል ልዩ የአስቸኳይ ጊዜ ማስተባበሪያ ክፍል ማቋቋም ይጠይቃል፡፡

4. ከማህበረሰቡና ከመገናኛ ብዙሃን ከፍተኛ ስጋት በሚንፀባረቅበት ሁኔታ ለደህንነት አደጋው የሚሰጠውን ምላሽና የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን ከፍ ወዳለ ደረጃ ማሳደግ ሊያስፈልግ ይቻላል፤

5. ባለስልጣኑ እንዳስፈላጊነቱ ለአደጋ ትንተና አስተባባሪ፣ የትኩረት ነጥብ፣ ግብረ ሀይል ይሰይማል፤ የአስቸኳይ ጊዜ ማስተባበሪያ ክፍል ያቋቁማል፡፡

6. ባለስልጣኑ እንዳስፈላጊነቱ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር ለአደጋ ትንተና ትብብር መሠረት ለመጣል መደበኛ የሆነ ቃልኪዳን ወይንም የመግባቢያ ሰነድ ይፈራረማል፡፡

7. ባለስልጣኑ ለአደጋ ትንተና የሚሆን ወጪ መሸፈኛ ገንዘብና ሌላም ግብዓት አቅርቦት ያመቻቻል፣ መኖሩን ያረጋግጣል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የመኖ ደህንነት አደጋ ግምገማ

## 9. የመኖ ደህንነት አደጋ ግምገማ መረጃ ክምችት ፋይል

1. ባለስልጣኑ ወጠታማና ፈጣን መረጃ ለማሰባሰብ የሚያግዝ የተቀናጀ የመረጃ ክምችት ፋይል ያደራጃል፡፡ ይህ ፋይል የሚከተሉት መረጃዎች ይኖሩታል፡-
   ሀ) በተጠቃሚዎች ላይ የሚኖሩ የጤና ወጤቶች፣ የጤና ችግሮቹ ክብደት፣ ምልክቶች፣ የህመሙ መገለጫ
   ለ) የአደጋ ግምገማ
   ሐ) በመኖ/ምግብ ሰንሰለት ወስጥ የማሰራጨት ዕድል፣ ወደ ሌሎች አስተዳደር ክልሎችና ሀገራት የማሰራጨት ዕድል
   መ) ክትትል ሊደረግበት የሚችልበት ደረጃ
   ሰ) የመኖው ምስል/ፎቶ፤ የክምችት ቁጥር/ ገላጭ ፅሁፍ
   ረ) ከምንጮቹ የሚገኝ ማንኛወም አግባብ ያለው መረጃ
   ሠ) ተዛማጅ ሳይንሳዊ መረጃ
   ሸ) የተጠቃሚ ምላሽ፣ የአደጋ ግንዛቤ፣ቅሬታ
   ቀ) በማናኛ ብዙሃን ላይ ያለው ተፅእኖ
   በ) ከመኖና ምግብ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት የተሰበሰቡ መረጃዎች
   ተ) ስለሌሎች ተመሳሳይ ክስተቶች የተሰበሰቡ መረጃዎችና በነዚህ ሁኔታዎች ስለተወሰዱ እርምጃዎች

## 10. የአደጋ ግምገማ ሂደት

1. የአንድ አደጋ ግምገማ የተፈፃሚነት ወሰንና ዓላማ በግልፅ መቀመጥና የሚሰበሰበው መረጃ ተለይቶ እንዲታወቅ ይደረጋል፡፡
2. የአደጋ ግምገማ ባለሞያዎች ግልፅ በሆነ መንገድ በችሎታቸወና በሳይንሳዊ ስራቸው ተዓሚኒነት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡ የወጭ ባለሞያዎችንና ድርጅቶችን ማሳተፍ አስፈላጊነትም በጥንቃቄ እንዲታይ ይደረጋል፡፡
3. የአደጋ ግምገማ በሳይንሳዊ መረጃ ላይ የተመሰረተና በተቻለ ማጠን ያለወን አሀዛዊና አሀዛዊ ያልሆነ መረጃ የማጠቀም ልምድ እንዲዳብር ይደረጋል፡፡ የግምገማው ዘዴ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካላቸው አካሄዶች ጋር የተጣጣመ ይሆናል፡፡
4. በኢንዱስትሪው ራሱ ወይንም በተቆጣጣሪ አካላት የሚከሄድ መደበኛ የመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ክትትል የሚይፈለጉ ነገሮች ይዘት ተቀባይነት ካለው ማጠን በላይ ያለመሆኑን ለማወቅ የናሙና ምርመራን ያካተተ ፍተሻ ይደረጋል፡፡
5. በአደጋ ግምገማ ሂደት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ወሰንነቶች በየደረጃው በተቻለ ማጠን በግልፅ ተመዝግበው ግምት ወስጥ እነዲገቡ ይደረጋል፡፡

6. የአደጋ ግምገማ ሂደት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተደራጅቶ የሚከተሉትን ደረጃዎች አካቶ መካሄድ አለበት፤ የጉዳት ምንጭ ልየታ፣ የጉዳት ምንጭ ባህሪ ግምገማ፣ የተጋላጭነት ግመምገማና የአደጋ ባህሪትንተና

## 10.1 የጉዳት ምንጭ ልየታ

1. በመኖ ወስጥ ሊኖሩ የሚችሉ የጉዳት ምንጮችን የመለየት ሥራ አካላዊ፣ ባዮሎጂያዊ ወይንም ኬሚካላዊ ሊሆኑ የሚችሉ ተፈላጊ ያልሆኑ ነገሮች እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡ በነዚህ ነገሮች የለወጥ ሂደት የሚፈጠሩ ሌሎች ወጤቶችም ግምት ወስጥ ገብተው ማካተት አለባቸው፡፡
2. የጉዳት ምንጭን ሙሉ በሙሉ መለየት በማይቻልበት ሁኔታ፣ ያሉ መረጃዎች ብቁ ሳይሆኑ ሲቀሩና እነዚህን ተፈላጊ መረጃዎችን ማመንጨት የሚያስችል ጊዜ ሳይኖር ሲቀር፤ በእጅ ያለን መረጃ ከባለሙያ አስተያየት ጋር በማቀናጀት እንደ ምትክ ጥቅም ላይ እንዲወል ይደረጋል፡፡
3. የጉዳት ምንጮችን የመለየት ሥራ እንደ ማምረት፣ ድረቅ፣ ማዘጋጀት፣ ከምችትና ማጓጓዝ ወቅት ያሉ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ምክንያት ከሌሎች አካላት ጋር ያለ ማስተጋብር በመኖ ወስጥ የጉዳት ምንጮች መኖር ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተፅእኖ ግምት ወስጥ ማስገባት አለበት፡፡
4. የጉዳት ምንጮችን የመለየት ሥራ ከተቆጣጣሪ አካላት የቅኝት ስራ፣ በመንግስት አካላት ከሚወጡ ህትመቶች፣ ሳይንሳዊ የህትመት ወጤቶች፣ የኢንዱስትሪ የወስጥ ክትትል ፕሮገራሞች፣ ወዘተ የሚገኙ ጠቃሚ የመረጃ ምንጮችን ግምት ወስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡
5. የትኞች የመኖ ጥሬ ዕቃዎች የችግር ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ መለየት እንዲያስችል የጥሬ ዕቃዎቹ ምንጮች ግምገማና የአካባቢያዊ ሁኔታ ጋር ሊኖር የሚችል ማስተጋብር፣ በምርት ሂደት፣ ዝግጅት፣ ማጓጓዝ፣ ከምችት፣ አጠቃቀም ወቅት በአደጋ ምንጭ የማበከል ዕድል ግምት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## 10.2 የጉዳት ምንጭ ባህሪ ትንተና

1. የጤና እክል የሚያስከትሉ ማናቸወም ከመኖ ጋር ይያያዛሉ ተብለው የተለዩ የጉዳት ምንጮች፣የተፈጥሮ ዑደት ወጤቶችን ጨምሮ አሀዛዊና ዓይነታዊ ግምገማ እንዲካሄድ ይደረጋል፤
2. ለጉዳት ምንጮች ግምገማ የሚሆን መረጃ ከዓለም አቀፍ ሪፖርቶች፣ የአደጋ ግምገማ ወጤቶች፣ ሳይንሳዊ የህትመት ወጤቶች ሊገኝ ይችላል፡፡ ይህ ጥቅም ላይ የዋለ መረጃ በአግባቡ ተመዝግቦ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡
3. በእጅ ላይ ያሉ መረጃዎች የጉዳት ምንጭን ሙሉ በሙሉ ለመገምገም ብቁ ሳይሆኑ ሲቀሩ ተፈላጊ መረጃዎችን ማመንጨት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ ማንኛወም ተጨማሪ መረጃ የማመንጨት ሂደት ሳይንሳዊ መርሆዎችን የተከተለእንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 10.3 የተጋላጭነት ግምገማ

1. ለአደጋ ምንጭ ተጋላጭነት የሚካሄድ ግምገማ በሁለት ደረጃ እንዲከናወን ይደረጋል ፡፡ የመጀመሪያው ደረጃ እንስሳት በመኖ በኩል ለአደጋ ምንጩ ያላቸወን ተጋላጭነት ይመለከታል፡፡

2. ሁለተኛው ደረጃ ለአደጋ ምንጩ ከተጋለጡ እንስሳት ወደሚገኝና ለሰው ምግብነት የሚውል የእንስሳት ተዋፅዖ የመተላለፍ ሂደት ላይ ያተኩራል፡፡

   ሀ) የእንስሳት ተጋላጭነት ግምገማ የሚወጣ ዝግጅት፣ አመጋገብና በዚህ ሂደት የሚኖር የመጋለጥ ሁኔታ ማካተት አለበት፡፡

   ለ) ለአደጋ ምንጩ ከተጋለጡ እንስሳት ወደሚገኝና ለሰው ምግብነት የሚውል የእንስሳት ተዋፅዖ ያለው የመተላለፍ ሂደት ግምገማ ተገቢውን ሥርዓት ተከትሎ መፈፀም አለበት፡፡

3. ከመኖ ወደ እንስሳትና ከተጋለጡ እንስሳት ወደሚገኝ ለሰው ምግብነት የሚውል የእንስሳት ተዋፅዖ ላለው የመተላለፍ ሂደት ግምገማ ከተለያዩ አግባብነት ካላቸው የሳይንስ ውጤቶች እንዲሁም ይህንን ለመተንበይ የሚያግዙ ሞዴሎች ለሁኔታው እንዲስማሙ በማድረግ ማጠቀም ይቻላል፡፡ ይህ ጥቅም ላይ የዋለ መረጃና ሞዴል በአግባቡ ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

## 11 የአደጋ ባህሪትንተና

1. የመኖ ደህንነት አደጋ ግምት ከመኖ ጋር የተያያዘ የአደጋ ባህሪ ትንተና የአደጋ ምንጩ ባህሪና የተጋላጭነት ግምገማ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ ይሰላል፡፡

2. የመኖ ደህንነት አደጋ ግምት በመኖ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የአደጋ ምንጭ መጠንና ደረጃ ካሉ ሀገራዊና ዓላምአቀፋዊ ከፍተኛ ማጠንና ደረጃ ጋር በማነፃፀር ይሰራል፡፡

3. የአደጋ ምንጩ እንደ ውሃና አየር ያሉ ከባቢያዊ አካላት ውስጥም የሚኖር ከሆነ ለአደጋ ግምገማና የክስተቱ አያያዝ በነዚህ ምንጮችም ላይ ተጨማሪ የተጋላጭነት ግምገማ ማካሄድን ታሳቢ ማድረግ አለበት፡
:

## 12 ሪፖርት ስለማቅረብ

1. የአደጋ ግምገማ ውጤት በተሟላ ሁኔታና በሥርዓት ተመዝግቦ እንደ አግባብነቱ በባለስልጣኑ ለተሰየመ ባለሙያ፣ ግብረሃይል ወይንም አስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ክፍል ሪፖርት ይደረጋል፡፡

2. የአደጋ ግምገማ ሪፖርቱ ያጋጠሙ ችግሮችን፣ አጠራጣሪ ሁኔታዎችን፣ የተወሰዱ ግምቶችንና ስለሚኖራቸው ተፅእኖ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡ በቡድን የሚሰራ ከሆነ የአናሳ አባላት ሀሳብም በሪፖርቱ መመዝገብ አለበት፡፡በሚወሰድ ቀጣይ እርምጃ የነዚህን ተፅእኖዎች በማገናዘብ መተግበር በባለስልጣኑ የተሰየመ ባለሙያ፣ ግብረሃይል ወይንም አስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ክፍል ሀላፊነት ይሆናል፡፡

3. የአደጋ ግምገማው ውጤት ለሌሎች ገምጋሚዎችና የሚመለከታቸው አካላት ሀሳብ እንዲሰጡበት ግልፅ ይደረጋል፡፡

# <u>ክፍል አራት</u>

# የመኖ ደህንነት አደጋክስተት አመራር/አስተዳደር

# 11. የመኖ ደህንነት አደጋክስተት አመራር/አስተዳደር

## 1. አጠቃላይ ታሳቢዎች

1. **ዝግጁነት፡ -** ምንም የመኖ ደህንነት ክስተት በሌለበት ወቅት እርምጃዎች በአጭር ጊዜ ለማስጥባቸው የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች ባለስልጣኑ ራሱን ያዘጋጃል፡፡ ይህ ዝግጅት የሚከተሉትን ያካትታል፡ -

ሀ) የተለያዩ የመረጃ ማሰብሰቢያ ቅፆች፣ የወቅታዊ ሪፖርት ማዘጋጃ ናሙናዎች፣ የውሳኔ አሰጣጥ የዕዝ ሰንሰለት ንድፍ፤ ለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች የሚጠቅሙ ግልፅና ትክክለኛ የመረጃ ምንጮች ጥንቅር፤ የአደጋ ዓይነቶች መገለጫዎች፣ፍቺዎቻቸውና ምሳሌዎች፤ የመኖ ደህንነት አደጋ ደረጃ ካርታዎች፣ ለተለያዩ የአደጋ ዓይነቶች አግበባብ ያላቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎችና አተገባበራቸው፤ ለአደጋው ዓይነትና ደረጃ ለዓለም አቀፍ አካላትና መንግስታት ጭምር ተስማሚ የመረጃ ልውውጥ አካሄድ፤ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አስተዳደር ቡድን አባላት ተግባርና ሀላፊነት፤ ለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሚና ያላቸው አካላት ዝርዝርና የአድራሻ መግለጫ፡ የተሟላ መረጃ በሌለበት ሁኔታ በእጅ ላይ ያለ መረጃንና የአሰራር ልምድ መነሻ በማድረግ የአደጋ ክስተትን በፍጥነት ለመገምገም ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

ለ) የተለያዩ የደህንነት አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ኬሚካላዊ አካላት ወይም ማስሎቻቸው ስለሚያስከትሉት ውጤት የመረጃ ክምችት አለ፡፡ ስለነዚህ መረጃዎች መኖር ጥቅምና የአስተማማኝነት ሁኔታ ተከታታይ ስልጠናና መረጃ ልውውጥ የአደጋ ክስተት ሲያጋጥም ፈጣን ምላሽ ለማስጠት አቅም ያዳብራል፡፡

ሐ) ከተለያዩ ባለሞያዎች፣ ድርጅቶች፣ ሀገራት ተፈላጊ መረጃዎችንና ሌላም ትብብር ለማግኘት መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ግንኙነትና አጋርነት መመስረት ያስፈልጋል፡፡ የመግባቢያ ሰነድ መፈራረም የሚፈጠረውን ግንኙነትና አጋርነት መደበኛና ተቀባይነት ያለው ያደርገዋል፡፡

2. ባለስልጣኑ የአደጋ ግምገማ መረጃዎችንና ዕውቀት አዳዲስ ሳይንሳዊ መረጃና ዕውቀት በተገኘ ቁጥር በተከታታይ ይከልሳል፡፡
3. ባለስልጣኑ የአስቸኳይ የመኖ ደህንነት አደጋ በየእርከኑ የሚተገበር ወቅታዊ ምላሽ አሰጣጥ ዕቅድ ያደራጃል፡፡
4. ባለስልጣኑ ጥሩ የግብርና ሥርዓት፣ ንፅህናን የጠበቀ የአሠራር ሥርዓት፣ ጥሩ የአመራረት ሥርዓት እና የጉዳት ምንጭ ትንተናና ወሳኝ የቁጥጥር ነጥብ፣ የአደጋ መከሰትን መቀነስ የሚያስችሉ ዕቅዶችንና የአደጋ ግምገማን ሥራ የሚደግፉ መመሪያዎችና የመሳሰሉ ሌሎች ሰነዶችን ያዘጋጃል ወይንም እንዲዘጋጁ ያበረታታል፡፡
5. ባለስልጣኑ እንደ ማሕበራት ካሉ አግባብ ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ከመኖ ጋር የተያያዙ የደህንነት ክስተቶችን ለመቀነስ የሚያግዝ ከመኖ ምርት እስከ አጠቃቀም ባለው ሂደት ላሉ ተዋናዮች የጉዳት ምንጭ ትንተናና ወሳኝ የቁጥጥር ነጥብ አሠራርን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማበረታቻ፣ የቴክኒክ ድጋፍና፣ ስልጠና ይሰጣል፡፡

## 2. የአደጋክስተት አመራር/አስተዳደርአማራጮችን ማለየት

1. የአደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር ከአደጋ ግምገማ የሚገኝ ውጤትን፣ ሌሎች ከወቅቱ አደጋ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነገሮችን፣ የሚፈለገውን ዓላማ ለማሳካት የሚያግዙ ለጥንቃቄ የሚሆኑ መርሆዎችን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡

2. ካሉት የአደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር አማራጮች ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ አንድ ወይንም ከዚያ በላይ አማራጮች ለትግበራ ይመረጣሉ ፡፡
3. የሚመረጠው የአደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር አማራጭ ሊከሰት እንደሚችለው የጤና ችግር ክብደት፣ የመከሰት ዕድሉ፣ የተጠቂዎች ብዛት፣ መኖር ያለበት ሽፋን፣ የአማራጩ ወጪታማነት፣ ላይ ተመስርቶ ይመረጣል፡፡ እነዚህ አማራጮች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡ -

   ሀ) የተበከሉወይንምሊበከሉይችላሉተብለውየሚጠረጠሩምርቶችንማሰብሰብናማፈተሽ፣

   ለ) ቀጣይምርትናስርጭትንማቋረጥ፣

   ሐ) የሚመለከታቸውንውጤቶችበፈቃደኝነትወይንምበግዳጅከገበያእንዲወጡማድረግ፣

   መ) የህዝብማስታወቂያናማስጠንቀቂያማውጣት፣

   ሰ) ሌሎችብርቱየመረጃልውውጥስልቶችንማጠቀም፣

   ረ) የምርትውጤቶችንበቁጥጥርስርማዋል/መያዝ፣

   ሠ) የምርትውጤቶችለይየማሻሻልሥራመስራት፣

   ሸ) የምርትውጤቶችንማስወገድ/ማውደም፣

   ቀ) አጥፊዎችንለሕግማቅረብ፣
4. የማስፈፀም አቅም፣ ስለአደጋው የእርግጠኛነት ደረጃ፣ ማህበረሰቡ የሚጠብቀውና ያለው ግንዛቤ፣ የሕግ ድጋፍ ደረጃ፣ ለተመሳሳይ አደጋ ክስተቶች የሌሎች ሀገራት ልምድ፣ በግብይት ላይ የሚኖር ተፅዕኖ የአደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር አማራጮችን ለመለየት ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

## 3. የተለዩ የአደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር አማራጮችን ስለመተግበር

እንደሚተገበሩት የአደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር አማራጮች ሁኔታ የትግበራው ሥራ መንግስትን፣ የምግብ ኢንዱስትሪውን፣ ምግብ ተጠቃሚዎችን ባካተተ መልክ በተለያዩ አካላት ይተገበራል፡፡

## 4. ስለአደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደርእርምጃዎች ውጤት ክትትልና ግምገማ

1. የአደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር እርምጃዎችትግበራ የአደጋውን ምንጮችና አደጋውን የመቆጣጠር ወጪታማነት ላይ ክትትል በማካሄድ የተወሰዱት እርምጃዎች የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አለማምጣታቸውን በመለየት ሌሎች ተጨማሪ እርምጃዎች ማስፈለግ አለማስፈለጋቸውን መወሰን ያስችላል፡፡

2. አንድ የአደጋ ክስተት ካለፈ በኋላ የተተገበሩት የአመራር/አስተዳደር እርምጃዎችን ትግበራ ሂደት በማገምገም የተገኘውን ተሞክሮ ወደፊት ለሚከሰቱ ተመሳሳይ ክስተቶች የተሻለ ውጤታማ ሥራ ለማከናወን ማጠቀም ተገቢ ነው፡፡

## 5. የመካከለኛና ከፍተኛ የመኖ ደህንነት አደጋ ክስተቶች አመራር/አስተዳደር

1. በእጅ ያለ መረጃ በጤና ላይ አላስፈላጊ ችግር ሊከሰት እንደሚችል አመላካች ሲሆንና አጠቃላይና ሰፊ እርምጃ መውሰድ የሚያስችል በቂ ሳይንሳዊ መረጃ ሳይኖር ሲቀር ሳይንሳዊ መረጃው እስከሚገኝ ድረስ በጤና ላይ ሊከሰት የሚችልን አላስፈላጊ ውጤት መቀነስ የሚያስችሉ ጊዜያዊ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

2. የሚወሰዱት ጊዜያዊ እርምጃዎች ለሁኔታው ተመጣጣኝ የሆኑና በንግድ እንቅስቃሴ ላይ አላስፈላጊ ማነቆ እንዳይፈጥሩ አግባብ ያላቸውን ቴክኒካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ሆነው ተፈላጊውን የጤና ከለላ ማስጠት የሚያስችሉ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

3. የሚወሰዱት ጊዜያዊ እርምጃዎች እንደ አደጋው ተፈጥሮና ያለውን የሳይንሳዊ መረጃ ክፍተት ለማሟላት የሚያስፈልገውን ጊዜ ግምት ወስጥ ባስገባ ሁኔታ በአጭር ጊዜ ወስጥ እንዲከለሱ ይደረጋል፡፡

## 6. የመካከለኛ ደረጃ የመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር

1. የመካከለኛ ደረጃ የመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደርና ወሳኔ አሰጣጥ በባለስልጣኑ የስልጣን ክልል ወስጥ ይፈፀማል፡፡ እንደ ግብረሃይል ማቋቋምና ከሌሎች ድርጅቶች ትብብር ማጠየቅን የመሳሰሉ ሁኔታውን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

2. በባለስልጣኑ የሚቋቋመው ግብረሃይል ለክስተቱ ምላሽ ለማስጠት በሌሎች ባለስልጣናት፣ ባለድርሻ አካላት፣ ላቦራቶሪዎችና ሌሎች መካከል ሊኖር የሚገባውን አስፈላጊ የቅንጅት ስራ የማምራት ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

3. የግብረኃይሉ አባላት ጥንቅርና የሥራ ዝርዝር እንደ ክስተቱ ዓይነት ሊለያይ ቢችልም የሥራ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማስረታዊ ተግባራት ያካትታል፡-

ሀ) የመረጃ ማሰባሰብና እንደ ሳይንሳዊ ፅሁፎች፣ የመኖ ፈጣን የማስጠንቀቂያ አሰጣጥ ሥርዓት፣ የንግድ መረጃ፣ የላቦራቶሪ ወጤቶችና ሌሎች አግባብ ያላቸውን የመረጃ ምንጮች በተማከለ መልክ ማደራጀት፤

ለ) ወቅታዊ ሁኔታውን የሚገልፁ የተሟሉ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት

ሐ) የሙያ ዝወወር ክትትል፤

መ) ወስጣዊ የመረጃ ልወውጥን ማስፋፋት፤

ሰ) ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለወን የመረጃ ልወውጥና ወይይት ማስፋፋት፤

ረ) የአደጋ መረጃ ልወውጥን ሚደራጀትና አግባብ ባላቸው የመረጃ ልወውጥ መንገዶች የሚደረግ ስርጭትን ማመቻቸት፤

ሠ) በጥራት ላይ የተመሰረተ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት (ወሳኔዎች፣ የተወሰዱ እርምጃዎች፣ የክትትል ሥራ፣ የተደረሰባቸው ድምዳሜዎች፣ የተገኙ ልምዶችና የመሳሰሉ መረጃዎች) ሚደራጀት፤

ሸ) የአደጋ ግምገማ ሥራን ማስተባበር፤

ቀ) ሳይንሳዊና የላቦራቶሪ ድጋፍ (ትክኒኮች፣ የናሙና አወሳሰድና የመሳሰሉ) ሥራዎች) ማስተባበር፤

በ) የሚወሰዱ እርምጃዎችን በተቀማጡ አሜልካቾች፣ ሪፖረቶች፣ የጥራት ደረጃዎችና አግባብነት ባላቸው መረጃዎች ላይ በመመስረት መከታተል፤

ተ) ለመገናኛ ብዙሃንና ተገልጋዮች የመረጃ አሰጣጥ ስትራተጂ መንደፍ፡፡

## 7. የከፍተኛ ደረጃ (የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ) የሙያ ደህንነት አደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደር

1. የከፍተኛ ደረጃ የሙያ ደህንነት አደጋ ክስተት አመራር/አስተዳደርና ወሳኔ አሰጣጥ በባለስልጣኑ የስልጣን ክልል ወስጥ ሊፈፀም ስለማይችልና ተጨማሪ ምላሽ ስለሚጠይቅ እራሱን የቻለ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ማስተባበርያ ክፍል ማቋቋምን ይጠይቃል፡፡ የማስተባበርያ ክፍሉ ከተለያዩ ባለሙያዎችና ማስሪያ ቤቶች የተወጣጡ አባላት ኖሮት ለክስተቱ የሚሰጠወን ምላሽ ለመምራት ሃላፊነት የተሰጠው አካል ሆኖ ይሰራል፡፡

2. በዚህ ደረጃ ላለ ክስተት የተገልጋዮች ግንዛቤና የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት ከፍተኛ ስለሚሆን ክፍሉ የተቀላጠፈ የመገናኛ ፖሊሲ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ የተለያዩና የሚጋጩ መልዕክቶች የመተላለፍን ዕድል ለማስወገድ በክፍሉ ወስጥ የተማከለ የወሳኔ አሰጣጥ በአግባቡ መተግበር አለበት፡፡

3. የማስተባበርያ ክፍሉ አባላት ጥንቅርና የሥራ ዝርዝር ፈጣንና ብቁ ወሳኔ ማስጠት እንዲያስችል ሆኖ በግልፅ ይደራጃል፡፡ የክፍሉ አባላት በሙያና ምግብ ዘርፍ ከፍተኛ ብቃትና ኃላፊነት የሚወስዱ ይሆናሉ፡፡

## 8. የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ማስተባበርያ ክፍልአባላት ጥንቅር

ሀ) የክፍሉ ሃላፊ፤

ለ) በሙያና ምግብ ሰንሰለት የተሰማሩ ድርጅቶች ተወካዮች፤

ሐ) በሕብረተሰብ ጤና የተሰማሩ ድርጅቶች ተወካዮች፤ መ) በኬላዎች የሙያ ቁጥጥር ላይ የተሰማሩ አካላት ተወካዮች፤

ሰ) አግባብ ያላቸው የሳይንስ ማህበረሰብና የላቦራቶሪዎች ተወካዮች፤

ረ) አግባብ ያላቸው የብሄራዊ/ክልላዊ ባለስልጣናት ተወካዮች፤

ሠ) የኮሚኬሽን ባለሞያ፤

ሸ) የሕግ ማማከር አገልግሎት፤

ቀ) እንደ ክስተቱ ሁኔታ አግባብ ያለው ሌላባለሞያ፣ የፖሊስና የጦር ሃይል፣ የአካባቢ የደህንነት አካላት፡፡

**9.የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ማስተባበርያ ክፍልተግባራት**

ሀ) የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ክስተትን በማየት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ፤

ለ) የላቦራቶሪ ድጋፍን ጨምሮ ተፈላጊው ሳይንሳዊ ድጋፍ መኖሩን ማረጋገጥ፤

ሐ) ችግር በተከሰተባቸው አካባቢዎች የመኖ አቅርቦት ሰንሰለት ሂደት ወስጥ ችግር የተከሰተባቸዉን ክምችቶች ምንጭ፣ ዝወወርና በመኖ ምርት ወቅት የችግሩ ተዛማችነት መረጃ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ አጥኚ አካል ማቋቋም፤

መ) ለመኖና ምግብ ደህንነት አግባብ ያላቸው ድርጅቶችን ተሳትፎ ማረጋገጥና የምላሹን አጠቃላይ የሥራ ሂደት ማስተባበር፤

ሰ) ለመኖናኛ ብዙሃንና ለተጠቃሚው ተገቢው መረጃ እንዳስፈላጊነቱ መድረሱን ለማረጋገጥ ተስማሚ የኮሚኬሽን ስትራተጂ መቅረፅ፤

ረ) ወቅታዊ ሁኔታን የሚገልፁ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት፤

ሠ) ቀደም ብሎ በተቀማጠ ማስፈርትና በወቅታዊ ሪፖርቶች ላይ ተመስርቶ በሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ ተከታታይ ክትትል ማድረግ፤

ሸ) እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ የገንዘብና የግብዓት ድጋፍ ማሰባሰብ፤

ቀ) በጥራት ላይ የተመሰረተ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት (ወሳኔዎች፣ የተወሰዱ እርምጃዎች፣ የክትትል ሥራ፣ የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች፣ ተሞክሮዎችና የመሳሰሉ መረጃዎች) ማደራጀት፤

በ) ተገቢ ሁኔታዎች ሲሟሉ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታው መወገዱን ይፋዊ መግለጫ እንዲሰጥ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

## ክፍል አምስት

## የመኖ ደህንነት አደጋክስተት ተግባቦት/ኮሚኬሽን

## 12. የአደጋ ክስተት ኮሚኬሽን

### 1.የመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት ኮሚኬሽን ታሳቢዎች

ባለስልጣኑ በመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት ወቅት በዓለምዓቀፍ ንግድ ምክንያት ችግሩ ሊነካቸው የሚችሉ የተለያዩ ሀገራትን ጨምሮ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት፣ ተባባሪዎች፣ ተፅእኖ የደረሰባቸው አካላት ወቅታዊና ግልፅ የመረጃ ልወውጥ ለማቅረብ የሚያስችል ስርዓት በቅድሚያ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በመኖ አደጋ ክስተት

ላይ የሚያተኩር ማንኛውም ምርምር እና የዳሰሳ ጥናት የሚካሄድ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ አካል፣ ስላካሄዳቸዉ የጥናትና ምርምር ዉጤቶች ባለሥልጣኑን ሳያስወቅ እና ያለባለሥልጣኑ የሕዝብ ግንኙነት እወቅና ለሕዝብ ይፋ ሚድረግአይገባዉም፡፡ለዚህም ተግባራዊነትከባለሥልጣኑ ጋር በቅድሚያየመግባቢያ ሰነድ ሚፈራረምና በአግባቡ ሚፈጸም ይጠበቅበታል፡፡

## 2. በመደበኛ ሁኔታ ስለሚኖር የመረጃ ልውውጥ

1. የመረጃ ልውውጥ ፖሊሲ በባለስልጣኑና በባለድርሻ አካላት መካከል መተማመንና ግልፅነትን ማስፈን የሚያስችል እንዲሆን በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በምክክር ይነደፋል
2. የአደጋ ግምገማ ወጤቶች በየወቅቱ ይፋ ይደረጋሉ፣ የመረጃ ልውውጥ ማስመሮችን ሁሉ ክፍት ይሆናሉ
3. ባለስልጣኑ የሚያስተላልፋቸው መልዕክቶች ለታለሚላቸው አካላት በትክክል መተላለፋቸውንና የሚፈለገውን ወጤት ማምጣታቸውን ለማረጋገጥ ጥናት ያካሂዳል

## 3. በመካከለኛና በከፍተኛ የመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት ወቅት ስለሚኖር የመረጃ ልውውጥ አጠቃላይ መምሪያ

1. በከፍተኛ የመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት ወቅት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚኖር የመረጃ ልውውጥ ስለሚጨምር ልውውጡ ከመደበኛው ሁኔታ በበለጠ ማዘውተር አለበት፡፡
2. በመካከለኛና ከፍተኛ ክስተት ወቅት ከመገናኛ ብዙሃን፣ ለችግሩ ከተጋለጡ አካላትና ከአጠቃላይ ሕዝቡ ጋር የሚደረግ የመረጃ ልውውጥን ተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጥፋትን የሚያስከትሉ እንዲሁም የተጠቃሚን እምነት የሚያሳጡ አላስፈላጊ ስህተቶችን ለማስወገድ ከሌሎች ተመሳሳይ መመሪያዎችና አሰራሮች ጋር ማጣጣም ያስፈልጋል፡፡
3. የመረጃ ልውውጥ ስራው የሚመራው እንደሁኔታው በግብረሃይሉ አስተባባሪ (ለመካከለኛ ደረጃ ክስተት) ወይንም በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ክፍሉ ሃላፊ (ለከፍተኛ ደረጃ ክስተት) ይሆናል፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች የሚተገበሩት አጠቃላይ መምሪያዎች የሚከተሉትን ማካተት ይኖርባቸዋል፡-
   - ሀ) የመረጃ ልውውጥ ስትራቴጂው እንደሁኔታው በግብረሃይሉ አስተባባሪ ወይንም በየአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ክፍል ሃላፊው ስምምነት የተደረሰበትና በቅርብ ትብብርና ቅንጅት መተግበር አለበት፤
   - ለ) የመረጃ ፍሰትን ወጥነት ለማረጋገጥና መደናገርን ለማስወገድ ማንኛውም የአደጋ መረጃ ልውውጥ በአንድ ግለሰብ ወይንም ቢሮ መመራት አለበት፤
   - ሐ) የመረጃ ልውውጥ አግባብ ያላቸው ባለድርሻ አካላት በሰየሙቸው ይፋ የግንኙነት ነጥቦች መካከል ይሆናል፤
   - መ) በሚሰጠው መረጃ ወስጥ የሚካተቱ መልዕክቶች ተጨማሪ መረጃ በተገኘ ቁጥር ወይንም ሁኔታው ሙሉ በሙሉ ግልፅ ባልሆነበት ሁኔታ መወሰድ ባለበት አስፈላጊ እርምጃ ሊለወጥ ይችላል፤
   - ሰ) መረጃው እንዲደርሰው ለተፈለገው አካል ተገቢው መልእክት መድረሱን ለማረጋገጥ በጉዳዩ ተፈላጊው ዕወቀት ያለውን ባለሙያ በአስቸኳይ የአደጋ ምላሽ ሰጪ ቡድኑ ወስጥ በማካተት ቡድኑ ሙያዊ ድጋፍ ማግኘት ይኖርበታል፤
   - ረ) የመኖ ደሕንነት አደጋ መረጃ ልውውጥ በሁለት አቅጣጫ የሚካሄድ መሆን አለበት፡፡ ባለስልጣኑ ከተለያዩ ምንጮች መረጃ የሚያገኝበትንና መረጃ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለማሳለጥ የመረጃ ልውውጥ ልዩ የስልክ ማስመር፣ የጥሪ ማዕከል፣ ድረገፅና የመሳሰሉ አሰራሮችን ማመቻቸት አለበት፤

ሠ) ያልተረጋገጠ መረጃ እንዳይተላለፍ ልዩ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የመረጃው መተላለፍ አደጋን ለመከላከል አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት ያለውን የመረጃ ክፍተትንም ጭምር በግልፅ ከመረጃው ጋር ማስተላለፍ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ በቂ መረጃ ያለመኖር መረጃውን ላለማስተላለፍ በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

4. የመረጃ ፍሰቱ ግልፅ መሆንና ለችግሩ የሚሰጠውን ምላሽ በተከታታይ ለመገምገም እንዲቻል በክስተቱ ሂደት ወቅት በሙሉ መቀጠል አለበት፡፡

5. የሚሰጠው መረጃ ስለ ክስተቱ ተፈጥሮና ስፋት ግልፅና የተሟላ መረጃ የሚሰጥ ሆኖ በተቻለ ማጠን የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

   ሀ) ስለ ምግብ ደህንነት አደጋው በወቅቱ ያለውን ዕውቀት፣

   ለ) የተጠቁት የምግብ ዓይነቶች፣

   ሐ) የተከሰተው አደጋ ዓይነትና ቦታው፣

   መ) ጉዳት የሚያስከትለው የተጋላጭነት ደረጃ፣

   ሰ) በመጋለጥ ወቅት እንዲወሰዱ የሚመከሩ እርምጃዎች፣

   ረ) የተጨማሪ መረጃ ምንጮችና የሚገኙባቸው መንገዶች፡፡

6. ከፍተኛ የምግብ ደህንነት አደጋ መከሰቱ ሲታወቅና አደጋው ከሀገሪቱ ክልል ወጪ ሄዶል ተብሎ ሲጠረጠር ባለስልጣኑ በችግሩ ማጠቃታቸው ለታወቁና ሊጠቁ ለሚችሉ ሀገራት እንደአግባብነቱ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፡፡ መረጃው የሚከተሉትን ያካትታል፡-

   ሀ) የታወቀው የአደጋ ምንጭን ሁኔታ፣ አደጋውን፣ ጥቅም ላይ የዋለው ስነዘዴና የተወሰዱ ግምቶችን ያካተተ የከፍተኛ የምግብ ደህንነት ሁኔታው ተፈጥሮ መግለጫ

   ለ) የተጠቁ የምግብ ዓይነቶች መለያ ምልክቶችን፣ ምስክር ወረቀትን ያካተተ መረጃ፤

   ሐ) የተጠቁና ሊጠቁ የሚችሉ አካላት፤

   መ) የላኪው፣ የአስገቢው፣ የአጓጓዡ ስምና አድራሻን የመሳሰሉ ከጉዞ ጋር ተያያዥ መረጃዎች፤

   ሰ) የአደጋ ምንጩን ለመቀነስ ወይንም ለማስወገድ የተወሰዱ እርምጃዎች፤

   ረ) ስለተሰየመ የሚመለከተው ሃላፊ፣ የግንኙነት ነጥብ፣ አግባብ ያለው ባለስልጣን፣ ዝርዝር ማብራሪያ፡ ፡

## 4. የመረጃ ልውውጥ መንገዶች

1. መረጃ ማግኘት ላለባቸው አካላት በሙሉ መረጃ መድረሱን ለማረጋገጥ አንድ የመረጃ ማስተላለፊያ መንገድ ብቻ ብቁ ላይሆን ይቻላል

2. የመረጃ ማስተላለፊያ መሣሪያውና መረጃው የሚቀርብበት መንገድ ለታለመለት ተቀባይ አካል እንዲስማማ ሆኖበክስተቱ ዋነኛ ተጋላጭ የሆኑ አካላትን ትምህርት ደረጃና የሚናገሩትን ቋንቋ ባገናዘበ መልክየተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

3. በተቻለ ማጠን የተለያዩ ተገቢነት ያላቸው የመረጃ ስርጭት መንገዶችን ማጠቀም ተገቢ ነው፡፡ እነዚህ መንገዶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

ሀ) ሬድዮ፣ ቴሌቪዥንና የህትመት ውጤቶች፤

ለ) ይፋዊ ጋዜጣዊ መግለጫ ኮንፈረንሶች፤

ሐ) የተባባሪዎችና ባለድርሻ አካላት የግንኙነት መረብ፤

መ) ስብሰባዎች፣ አወደጥናቶች፣ የቡድን ግንኙነቶች፤

ሰ)የመረጃ ማስጫ መድረኮች፤

ረ) ኢንተርኔት አገልግሎት፡- በድረገፆች ላይ በማስጠፍ፣ የማሕበራዊ ድረገፆችን (ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ወዘተ) በማጠቀም፤

ሠ) የማስከ ሠራተኞችንና ድርጅቶችን በማጠቀም፤

ሸ) ለተጠቃሚ መረጃ ማስጫ ልዩ የስልክ ማስመሮችን፣ ልዩ የስልክ አፕሊኬሽኖችን ማጠቀም፡፡

## 5. ስለሚሰጥ መግለጫ ይዘት

1. በከፍተኛ የመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት ወቅት የሚሰጥ መግለጫ ወስጥ የሚተላለፍ መልዕክት ለተጠቃሚዎች ግልፅ መሆኑን ለማረጋገጥ ልዩ ጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል፤
2. የመግለጫው ይዘት አላስፈላጊ ድንጋጤና መረበሽ ሳይፈጥር የሚፈለገውን መልዕክት ማስተላለፍ መቻል አለበት፤
3. የመረጃው ተጠቃሚ ተፈላጊ አማራጭ እርምጃዎችን መወሰድ የሚያስችለው በቂ መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡፡ ይህ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

ሀ) ስለ አደጋው ተፈጥሮ፣ ባህሪ፣ ወዘተ፣ ገላጭ መረጃ፤

ለ) ችግሩ የተከሰተባቸው የምርት ወጤቶች እንደ ምስል/ፎቶ/ የጥቅል ቁጥር/ገላጭ ፅሁፎች፣ የስርጭት ማስመሮች የሚሳሰሉ ገላጭ መረጃዎች፤

ሐ) በተጠቃሚዎች ላይ የሚኖረው የጤና እክል መግለጫ (ተጠቂ አካላት፣ የሚገኙበታቸው አካባቢዎች፣ የጤና ችግሮቹ መግለጫ የመረጃው ምንጮች)

መ) የተወሰዱና የታቀዱ እርምጃዎች፤

ሰ) የደህንነት ችግሩ ያለበት መኖ በእጃቸው ያለ አካላት መወሰድ ያለባቸው እርምጃ፤

ረ) የደህንነት ችግሩ ያለበትን መኖ ለእንስሶቻቸው የመገቡ መወሰድ ያለባቸው እርምጃ፤

ሠ) ለመረጃ ልወውጥና ለጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ጠቃሚ የስልክ፣ የድረገፅ፣ የኢሜይል አድራሻ፣ የፋክስ ቁጥር መረጃዎች፡፡

# ክፍል ስድስት

## የመኖ ደህንነት አደጋ ትንተና፣ ክትትልና ግምገማ

## 13. ክትትልና ግምገማ

1. በመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት ሂደት ለክትትልና ግምገማ ተግባር የሚያገለግል ዝርዝር መረጃ እንዲያዝ ይደረጋል፤
2. በመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት ሂደት የክስተቱን አያያዝና የመረጃ ልወውጥ እንቅስቃሴዎች ላይ ተከታታይ ግምገማ በማካሄድ ወቅታዊ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይደረጋል ፤
3. አንድ የመኖ ደህንነት አደጋ በተለይ የመካከለኛና የከፍተኛ ክስተት ሲያልቅ የሙሉው ክስተት ሂደት ግምገማና ትንተና ላይ የተመሰረተና የተወሰዱ ትምህርቶችንና ምክረ-ሃሳቦችን የያዘ ሪፖርት ይጠናቀራል፡፡ ሪፖርቱ የሚከተሉትን ጉዳዮች ይይዛል፡-

ሀ)የመረጃ ፋይል ግምገማውጤት፣

ለ)የክስተቱ አስተዳደር ግምገማወጤት፣
ሐ)ከተጠቃሚ ከማናኛ ብዙሃን ጋር ስለነበረ የመረጃ ልውውጥ ግምገማግብረ መልስ፣
መ)የክትትል ሥራዎች ግምገማወጤት፣
ሰ)የውስጥ አሠራር ሥርዓት ግምገማውጤት፡፡

## 14. የመኖ ደህንነት አደጋ ትንተና እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት

1. የፍተሻና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት የባለሥልጣኑ የመኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የምዝገባና የሥራ ፈቃድ ማሰጫ አሠራር መመሪያ 02/2018 መሠረት ይተገበራል፡፡ የመኖ አደጋ ትንተና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡትን የአሠራር ሥርዓቶች በመጠቀም የሚከተሉትን ግምት ውስጥ በማስገባት ተፈፃሚ ይሆናል
   ሀ) የመኖ ደህንነትን ለማረጋገጥ ተግባራዊ የሚደረግ የፍተሻና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት ለአደጋው ግምገማ ሁኔታ ተስማሚ በወቅቱ ባለው ሳይንሳዊ መረጃ ላይ ተመስርቶ መቀረፅና መተግበር አለበት፤
   ለ)በማንኛውም የመኖ ማምረትና ስርጭት ሰንሰለት ሊኖር የሚችል ለእንስሳትና ሕብረተሰብ ጤና የአደጋ ምንጭ ላይ ያተኮረ ተከታታይና ግልፅ የአደጋ ትንተና በማካሄድ በመኖ ደህንነትና የፍተሻ ሥርዓቱ ላይ በተዋናዮች መካከል መተማመን እንዲኖር በማድረግ  የንግድ ልውውጥን ማሳደግ በሚያስችል መልክ ይተገበራል፤
   ሐ).ባለስልጣኑ ከመደበኛው ፍተሻ በተጨማሪ የደህንነት አደጋ ይኖራል ተብሎ በተጠረጠረ ቦታና ጊዜ የግምገማ ሥራ ይሠራል፤
2. የሚፈለገውን የአመራረት፣ ክምችትና ማጓጓዝ ደረጃ ለማሟላት እንዲያግዝ የመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራቾችና ሌሎች ተዛማጅ የኢንዱስትሪው ዘርፎች የራሳቸውን የውስጥ ቁጥጥር ሥራ እንዲያካሂዱ ይበረታታሉ፡፡ መደበኛ ተቆጣጣሪዎች የጉዳት ምንጭ ትንተናና ወሳኝ የቁጥጥር ነጥብ መርሆዎች ተግባራዊነት የመገምገም መደበኛ ስልጠና ይሰጣቸዋል፤
3. የግምገማ ውጤቶችን ወካይነትና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ደረጃዎችና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ዓለምአቀፍ ደረጃዎች መሠረት በተገቢው የናሙና አወሳሰድ ላይ ተመስርቶና የተረጋገጡ ዘዴዎችን በመጠቀም ይከናወናል፤
4. የአንድ ቁጥጥር ፕሮገራም እንደተገቢነቱ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤ ፍተሻ/ ኦዲት፣ ናሙና መውሰድና መመርመር፣ የግልና የአልባሳት ንፅህናን ያካተተ የጤና አጠባበቅ ፍተሻ፣ በፅሁፍና በሌላ መልክ የሚገኙ መረጃዎች፣ በተቋሙ የተካሄዱ የማረጋገጫ ስርዓት ውጤቶች በመመርመር፣ ባለስልጣኑ በተቋሙ ላይ ቀደም ሲል ያካሐየዳቸው ግምገመማ ወጤቶች፣ የቁጥጥር ፕሮግራሙ ብሔራዊ ግምገማ ወጤት፤
5. በቁጥጥር ሥርዓቱ ችግር አለባቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ሁኔታዎችንም ጨምሮ ተፈላጊው ቁጥጥር መካሄዱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አስተዳደራዊ አሰራር መኖር አለበት፤
6. እንደተገቢነቱ የቁጥጥር ሥራው የሚከተሉትን መሸፈን አለበት፤ የሚመለከታቸውን ተቋማት፣ ድጅቶች፣ ማጓጓዣዎች፣ ቁሳቁስና መሳሪያዎች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ ግብዓቶች፣ ለመኖ ዝግጅትና ምርት የሚውሉ አጋዥ የቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ያለቀላቸውና ያላለቀላቸው ውጤቶች፣ ከመኖ ጋር ንክኪ የሚኖራቸው ቁሳቁሶች፣

የፅዳትና ለጥገና ሥራ የሚውሉ ወጤቶችና ፀረ ተባዮች፣ መኖን የሚፈብረክና የማዘጋጀት ሂደቶች፣ የጠና የደረጃ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት ተአሚኒነት፣ የማቆያ ዘዴዎች፣ የገላጭ ፅሁፎች ተአሚኒነት፡፡

## ክፍል ሰባት

## ለመኖ ደህንነት አደጋ ትንተና ድጋፍ የአቅም ግንባታ

### 15. የባለስልጣኑን አቅም ስለማንባት

1. ባለስልጣኑ የሰው ሃይልና የመሠረተ ልማት አቅሙን በሚተሽና ክፍተቶችን በማየት የሚጠበቅበትን የመኖ ደህንነት አጠባበቅና የደህንነት አደጋ ሲከሰት አስፈላጊውን ምላሽ የማስጠት ተግባርና ሀላፊነት በተፈላጊ ደረጃ ለመወጣት የሚያስችል አቅም እንዲገነባ ይደረጋል፤
2. የመኖ ደህንነት አደጋ ትንታኔና የመኖ ደህንነት የማጠበቅ ተግባርን ተቋማዊ ለማድረግ የባለስልጣኑን የቴክኒክ ብቃትና የመሠረተ ልማት አቅም ማንባት ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ በዚህ ረገድ የሚከተሉት እርምጃዎች ዋነኞቹ ይሆናሉ፡ –

    ሀ)አግባብ ያላቸውን የባለስልጣኑን ሠራተኞች በአደጋ ግምገማ፣ አመራር/አስተዳደርና መረጃ ልውውጥ ላይ ያላቸውን ክህሎትና እውቀት መደበኛ ስልጠና፣ የሥራ ላይ ስልጠናናየልምድ ልውውጥ በመሳሰሉ ዘዴዎች ማንባት፤

    ለ) የባለስልጣኑን አቅም በመረጃ ቴክኖሎጂ፣ መገናኛ፣ ላቦራቶሪ አቅምና መጓጓዣን ጨምሮ ለተለያዩ የመኖ ደህንነት አደጋ ክስተት ፈጣን ምላሽ ማስጠት ተፈላጊ በሆኑ ቁሳቁሶች ማደራጀት፡፡

### 16. የባለድርሻ አካላትን አቅም ስለማንባት

1. ባለስልጣኑ በመኖ ማምረትና አጠቃቀም ሂደት የተሰማሩ የኢንዱስትሪ፣ የግብርና፣ የንግድ ሥራ ተዋናዮችን ያካተተ የባለድርሻ አካላትና አጠቃላይ ሕብረተሰቡ በመኖ ደህንነት ላይ ያላቸውን ዕውቀትና ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ የትምህርትና ስልጠናን አስፈላጊነት ትልቅ ግምት በማስጠት ይደግፋል፤
2. የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲሁም በኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ያለውን አቅም በማንቀሳቀስ በተግባራዊ ስልጠና አሰጣጥ እንዲያግዙ ያደርጋል፤
3. ባለድርሻ አካላትን ማግኘት የሚያስችሉ እንደ ድረገፆችን፣ ስብሰባዎችን የመሳሰሉ ዕድሎችን ሁሉ በማጠቀም በመኖ ደህንነት ላይ የአቅም ግንባታ ሥራ ይሰራል፤
4. የመኖ ኢንዱስትሪዎች የራሳቸውን ውስጣዊ የመኖ ደህንነትና ጥራት የማከታተልና የሚረጋገጥ አቅማቸውን በማጠናከር በመኖ ደህንነት ማረጋገጥ ተግባር ሜኑቸውን እንዲወጡ እገዛ ይደረጋል፡፡

## ክፍልስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17. ተፈፃሚነት ስለሚዩኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ሰርኩላር፣ደብዳቤ፣የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፤

## 18. መመሪያውን ስለማሻሻል

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት ጊዜ ይህን መመሪያ እንደገና ማሻሻል ይችላል፡፡

## 19. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ____________ ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ጠርዙ ዳያ ደጋጋ(ዶ/ር)**

**የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር**
**ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር**